ሐጅና ዑምራን አከታትላችሁ አድርጉ። ወናፍ የብረትን፣ የወርቅንና የብርን ቆሻሻ እንደሚያስወግደው እነርሱም ድህነትንና ወንጀልን ያስወግዳሉ። ተቀባይነት ላለው ሐጅ ከጀነት በቀር ሌላ ምንም ምንዳ የለውም።

ከዓብደላህ ቢን መስዑድ ረዺየሏሁ ዐንሁ - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው እንዲህ አሉ: «የአላህ መልክተኛ ሶለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም -የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና- እንዲህ ብለዋል: "ሐጅና ዑምራን አከታትላችሁ አድርጉ።
ወናፍ የብረትን፣ የወርቅንና የብርን ቆሻሻ እንደሚያስወግደው እነርሱም ድህነትንና ወንጀልን ያስወግዳሉ። ተቀባይነት ላለው ሐጅ
ከጀነት በቀር ሌላ ምንም ምንዳ የለውም።"»
[رواه الترمذي والنسائي وأحمد] [ነው። ሶሒሕ[

ነቢዩ ሶለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም -የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና- የሐጅና የዑምራን አምልኮ አቀራርቦ በመፈፀምና ከቻሉ ሳያቆራርጡ በመፈፀም ላይ አነሳሱ። ምክንያቱንም ሲገልፁ ብረትን በወናፍ እሳት መንፋት ብረቱ ላይ የተቀላቀለውን ባዕድ የማዕድን ቆሻሻ ለማስወገድ ምክንያት እንደሆነው ሁሉ እነርሱንም መፈፀም ድህነትንና ወንጀልን እንዲሁም ወንጀል በቀልብ ላይ የሚኖረውን ተፅዕኖ ለማስወገድ ምክንያት መሆናቸውንም ገለፁ።

http://www.sunnah.global/hadeeth/am/show/65627